# አዲስ የንግድ ቦታዎን መክፈት

አንድ የእድሳት ወይም የግንባታ ፕሮጀክት እንዴት ማጠናቀቅ እንደሚችሉ እና በሲያትል ውስጥ በአካል የሚገኝ ንግድ እንዴት እንደሚከፍቱ ይወቁ። ይህ መመሪያ አዲስ የንግድ ቦታ ለመክፈት ወይም እንድ የንግድ ሥራን ለማደስ የሚያስፈልጉትን ደረጃዎች በዝርዝር ያስቀምጣል።



## ለፕሮጀክት ዕቅድ ማውጣት

የጊዜ መስመሮች እና ዋጋዎች በፕሮጀክትዎ ላይ የተመሠረተ ነው። ከታች የተዘረዘረው እንደ ሀሳብ የቀረበ የጊዜ መስመር ነው፣ ነገር ግን የእርስዎ ፕሮጀክት የበለጠ ወይም ያነሰ ጊዜ ሊወስድ ይችላል።

### ከመክፈት ቢያንስ ከአንድ አመት በፊት፦ ትክክለኛውን ቦታ ያግኙ

#### ቦታዎችን ማጥናት

- ተፈላጊነት ያለው ቦታ ለማግኘት የሚረዳዎትን አንድ የቤት ደላላ ያግኙ።
- በሚፈለጉት ቦታ አካባቢ ያሉትን የጎረቤት የንግድ ቡድን ያነጋግሩ።
- ለፕሮጀክትዎ ገንዘብ ያግኙ።
- ቦታው አሁኑ ባለው ፈቃድ እና በአድራሻው መሠረት ምን ጥቅም ላይ ሊውል እንደሚችል ለማወቅ ከሲያትል ከተማ ሰራተኛ ነፃ የጥናት እገዛ ያግኙ።

#### ውልዎን ይደራደሩ

- ስለ የፍላጎት ደብዳቤ ከባለንብረቱ ጋር ይነጋገሩ።
- ውልዎን ለመደራደር የሚረዳ ጠበቃ ያግኙ።
- እድሳቶች ምን ያህል እንደሚያስወጡ ግምት ለማውጣት አርኪቴክት ይቅጠሩ።
- ፊርማ ከማድረግዎ በፊት አንድ ጠበቃ ውልዎን እንዲያይ ያድርጉ።

### ከመከፈቱ ቢያንስ ዘጠኝ (9) ወራት በፊት፦ ፈቃዶችን ያግኙ

#### ንድፍ እና እቅድ

- ዕቅዶችን ከአርኪቴክትዎ ጋር ያጠናቅቁ።
- የቤት እቃዎች፣ የተገጣጠሙ እቃዎች፣ እና የመሳሪያ ዋጋዎችን ጨምሮ የዘመነ በጀት ያግኙ።

- ፈቃድ ካለው ተቋራጭ ጋር ይነጋገሩ እና የፕሮጀክት የጊዜ ሠሌዳ እና የወጪ ግምት ይፍጠሩ።

### ለፍቃዶች ያመልክቱ

- ለእርስዎ ምን ፍቃዶች እንደሚያስፈልጉ ለማወቅ ለፈቃድ ማሰልጠኛ ይመዝገቡ።
- የእርስዎ ንግድ በአንድ ታሪካዊ ወረዳ ወይም በታሪካዊ ምልክትነት ተጠብቆ የሚቆይ ሕንፃ ውስጥ ከሆነ፣ የታሪክ ማቆያ ማጽደቂያ የምስክር ወረቀት ያስፈልግዎታል
- ማንኛውንም ግንባታ ወይም እድሳት የሚሰሩ ከሆነ፣ አርኪቴክትዎ ለግንባታ ፈቃድ እንዲያመልክት ያድርጉ።
- የምግብ ንግድ እየከፈቱ ከሆነ፣ የምግብ አገልግሎት እቅድዎ በሕዝብ ጤና - ሲያትል እና የኪንግ ካውንቲ (PHSKC) የምግብ እና መገልገያዎች ፕሮግራም ያስገምግሙ።
- እንዲሁም በ ኪንግ ካውንቲ የቧንቧ ሥራ እና ጋዝ ፕሮግራም ፈቃድ ሊያስፈልግዎት ይችላል።
- እንደ መጠጥ ፈቃድ ወይም የንግድ ምልክት ፈቃድ ያሉ ለእርስዎ ንግድ አስፈላጊ በሆኑ ላይ በመመስረት ለሌሎች ፈቃዶች ያመልክቱ።

## ከመከፈቱ ከስድስት (6) ወራት በፊት፦ ግንባታ

- እርስዎ እና የሥራ ተቋራጭዎ ግንባታው ከመጀመሩ በፊት ሁሉንም ፈቃዶች እንዳለዎት ያረጋግጡ
- የግንባታውን የጊዜ ሠሌዳ ከሥራ ተቋራጭ ጋር ይመልከቱት
- እርስዎ ለየትኞቹ ምርመራዎች ቀጠሮ እንደሚያስይዙ እና የሥራ ተቋራጩ ለየትኞቹ ቀጠሮዎች እንደሚያስይዝ ይወቁ

## ከመከፈቱ ከሶስት (3) ወራት በፊት፦ ምርመራዎች

### ለምርመራዎች ቀጠሮ መያዝ

- ለግንባታ ስራዎች ከSeattle Department of Construction and Inspections (የሲያትል የግንባታ እና ምርመራዎች መምሪያ) እና ከሲያትል የእሳት አደጋ መከላከያ መምሪያ ምርመራዎችን ያግኙ።
- ሌሎች ማንኛቸውንም፣ ለምሳሌ እንደ ከ100+ ሰዎች ላሏቸው የምግብ ንግድ ቤቶች የመሰብሰቢያ ፈቃድ ያሉ ከሲያትል የእሳት አደጋ መምሪያ ሊፈልጉ የሚችሉትን ፈቃዶች ያግኙ
- አስፈላጊ ከሆነ፣ ከኪንግ ካውንቲ የህዝብ ጤና ለምግብ አገልግሎት እና የቧንቧ ሥራ እና የጋዝ ፍተሻዎችን ያግኙ።
- ከሁሉም ፍተሻዎች በኋላ፣ የእርስዎን የይዘት የምስክር ወረቀት ለመቀበል የመጨረሻ ፍተሻ/ምርመራ ያግኙ።

የሲያትል ከተማ፣ እያንዳንዱን ሰው በፕሮግራሞቹ እና በእንቅስቃሴዎቹ እንዲሳተፍ ያበረታታል። እርዳታ፣ ትርጉም፣ ለአካል ጉዳተኞች የሚደረጉ ማስተካከያዎች ወይም በተለየ ቅርጸት የተዘጋጁ ሰነዶች ከፈለጉ፣ ቢሮአችንን በ(206) 684-8090 ወይም በOED@seattle.gov ያነጋግሩ።